# <u>"ውሸትና ስንቅ እያደረ ይቀላል"</u>!!!

ከባህልቢ ዘማርያም

<u>ክፍል ሁለት፤</u>

ባለፈው ሳምንት የክቡር አባ ኃይለሚካኤል ወልደማርያምን የዘፈን ምርጫ በማስታወስ ነበር የዘጋነው። ስለሆነም፤ "አኑ ጉረም ሐቀ፤ ዲራቢሊ ጉረም ዮዋ ቲብ አከ" የሚለው ጊዜው እስኪፈቅድ ድረስ የዚህ ፀሐፊ መፈክር ሆኖ ይቀጥላል።

ባለፈው መጣጥፍ ውስጥ በተከታታይ ስለተካሄዱት የኢሮብ ተወላጆች የተለፎን ስብሰባዎችን በማስታወስ የታዩ ሕጸጾችን ለማመላከት ተሞክሯል። ዛሬም ቢሆን ይህ ፀሐፊ በነዛ ድክመቶች ላይ በማትኰር መጠነኛ አስተያየት ለመሰንዘር ይፈልጋል።

የሐጎስ ዮሐንስ የውንጀላ ፅሑፍን አስመልክቶ እውነቱ እንዲወጣ የስልክ ስብሰባ ላይ የተሳተፈው ህዝባችን ያደረገው አስተዋጽኦ እጅጉን የሚመሰገን ቢሆንም፤ ውንጀላው ባገባቡ መልስ ሳያገኝ እንዲሁ በእንጥልጥል እንዲቀር ችላ ተብሎ መተዉ ግን መታረም የሚገባው ጉልህ ድክመት ነው። ይህ ውንጀላ አንዱን ወይም ሌላውን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የጋራ ችግራችን ነው። ሐጎስ ዮሐንስ ተፈጸመ ያሉት ወንጀል በግለ-ሰብ ላይ የደረሰ በደል ሳይሆን በህብረተ-ሰብ ላይ የተፈጸመ አስከፊ ወንጀል ነው። በመሆኑም፤ ሐጎስ ዮሐንስ "ታማይ ዳ ማፋኪና ዱደ እድታነክ" ብለው እንዲሁ በሽወዳ እንዲያልፉት መፈቀድ አልነበረበትም። ደረሰ ያሉት ወንጀል ሁልችንን በጋራ የሚጎዳ፤ ለወደፊትም እጅግ አስቀያሚ እድምታ ትቶብን የሚያልፍ ቁስል መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት በተገባ ነበር። የዛሬ ሕፃናቶቻችን የነገ የሕብረተ-ሰብ ምሰሶዎች ለሻዓቢያ ቅጥረኞች የሚመለምሉ የኢሮብ ተወላጆች አሉ የሚለው፤ ሐጎስ ዮሐንስ ያቀረቡትን ወንጀል የፈጸመ ሰው ወይም ሰዎች ይህንን የትውልድ ቀጣይነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ወንጀል በመፈጸም ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ሁላችን በጋራ ሁነን ልንፋረዳቸው ይገባል። ይህንን ማድረግ አቅቶን ተፈጸመ የተባለውን ወንጀል እንዲቀጥል ከፈቀድን የመጀመርያ የታሪክ ተወቃሾች የምንሆነው እኛው የዚህ ትውልድ አባሎች መሆናችን ፈጽሞ መዘንጋት የለበትም። ስለሆነም፤ የዚህ ዓይነት አስከፊ ወንጀል በሕፃናቶቻችን ላይ ሲፈጸም የዳር ተመልካች ሁነን መቆም በፍርድ ቤት ላያስከስሰን ቢችልም ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን ግን ፈጽሞ አንችልም። ስለሆነም፤ ይህንን ዓይነት አስቀያሚ ወንጀል የሚፈጽሙ የኢሮብ ተወላጆች አሉ ብሎ በይፋ በድረ-ገጽ ጽፎ የበተነ ሰው አሉኝ የሚላቸው ተጨባጭ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ መጠየቅ የማይገሰስ መብታችን ነው። ማስረጃዎች ከቀረቡ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት በማቅረብ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ይቻላል።

ከዚህም በተቃራኒ፤ በቂ ማስረጃ ሳያቀርብ አሁን እንደታየው የማንንም ይሁን የማን የሰውን መልካም ስም ለማጉደፍ፤ ባልዋለበት በሕብረተ-ሰቡ ውስጥ እንደወንጀለኛ እንዲታይ በመቀስቀስና የሰዎች ስብእናን ለማበላሸት ሆን ተብሎ የሚፈጠር ወሬ የኋላ ኋላ የራሱ የሆነ መዘዝ ያስከትላል። የሕብረተ-ሰብን ፍትሐዊ አመለካከት ያዛባል፤ ልጆቻቸው ወደ ኤርትራ ክፍለሀገር የኮበለሉባቸው ቤተሰቦች በአስኮብላይነት የተወነጀሉ ወገኖች ቤተሰቦች ላይ ቂም ይቋጥራሉ። በዚህም ወገን ከወገን እየተለያየ አንዱ ሌላው ላይ የሚያሴርበት፤ ሕብረተ-ሰቡ በጥርጣሬ ዓይን የሚተያይበት ጤነኛ ያልሆነ ግንኙነት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል። ይህ ደግሞ የአንድን ሕብረተ-ሰብ ጤነኛ አብሮ የመኖር ግንኙት መሻከርን ያስከትላል። ድምር ውጤቱም ሁሉንም የሚጎዳ ሕብረተ-ሰባዊ ቀውስ መከሰት ይሆናል። ስለሆነም፤ ችግሩ በቸልታ መታየት የለበትም። ለወደፊት ይህ ዓይነት ቅጥፈት

የተሞላበት ተግባር እንዳይፈጸም ከተፈለገ፣ ውንጀላው እገሌን እንጂ እኔን ላይመለከት ይችላል ስለዚህም እኔ ምንቸገረኝ ወዘተ. በመሳሰሉ አጉል ምክኒያቶች ችላ ማለት ሳይሆን ጉዳዩን በሚገባ መርምረን ያሁኑን ክስተት እንደ ማስተማርያና ማስተካከያ ልንጠቀምበት ይገባ ነበር።

ወደ ተካሄዱት የስልክ ስብሰባዎች ስንመለስ፣ አንዳንድ ይህ ፀሐፊ ግንዛቤ የወሰደባቸው የሚያስተዛዝቡ ክስተቶች ነበሩ። ብዙሐኑ ምንም ይሁን ምን እውነቱ እንዲወጣ ጉግት እንደነበራቸው በግልጽ ታይቷል። ወደሚቀጥለው እርምጃ እንዲሸጋገሩ ሐጎስ ዮሐንስ አለኝ ያሉት ማስረጃ ይፋ እንዲያደርጉ ጠይቋል፣ ጎትጉቷል። ሐጎስ ዮሐንስ ግን ፍንክች ሳይሉ "ታማይ ዳ ማፋኪና ዱደ ኤታነክ" "ድንጋዩን አትክፈቱት ጉንዳን አለበት" ብለው ከመደጋገም ውጭ አንድም ማስረጃ ለማቅረብ ሳይችሉ ቀርቷል። "ታማይ ዳይ ፋኪቶይ ዱደ ታውፆይ" ድንጋዩ ይከፈት ጉንዳኑም ይውጣ" ተብለው ቢጠየቁም የሌለውን ነገር ማምጣት አይቻልምና ድንጋዩን ከፍተው "ጉንዳኑ" እንዲወጣ ለማድረግ አልቻሉም። እውነት እንዲወጣ የገፉ ወገኖች የሚያስመሰግን የሞራል ልዕልና ቢያሳዩም ሐጎስ ዮሐንስ ላወጡት ውንጀላ ማስረጃ ማቅረብ አለመቻላቸውን የሚያሳይ፣ እንዲህ ዓይነት ተግባር እንዳይደገም የሚያስጠነቅቅ የጋራ መግለጫ ለማውጣት ግን ሳይችሉ ቀርቷል።

ሆኖም በስልክ ስብሰባው ላይ የተሳተፈው ሁሉ እውነት እንዲወጣ ፍላጎት ነበረው ማለት አይደለም። የተወሰኑ ወገኖች እውነቱ እንዳይወጣ ይከላከሉ እንደነበረ ግልጽ ሆኖ ወጥቷል። ይህ ፀሐፊ ኋላ እንዳጣራው ሐጎስ ዮሐንስ ጥያቄውን እንዳይመልሱ ሲከላከሉ የነበሩ ወገኖች አብዛኞቹ የሥጋ ዘመዶቻቸው ናቸው። እየጠቀሟቸው መስሎዋቸው ይሆናል። ይህ ፀሐፊ እነሱ ቦታ ላይ ቢሆን ኖሮ፣ ገና ስለስብሰባ ሲወራ ጭብጥ ካለህ ጭብጡን አቅርብ፣ ከሌለህ ግን ባፋጣኝ ይቅርታ ጠይቅ ብሎ ነበር የሚመክራቸው። አላደረጉትም። በተቃራኒው ሐጎስ ዮሐንስ ላቀረቡት ውንጀላ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተሰብሳቢው ሲጠይቅ፣ ሐጎስ ዮሐንስን በመወገን ፍትሓዊ ሳይሆን ወገናዊ አቋም ሲወስዱ ተስተውሏል። ፍትሕ እንዲህ በወገናዊነት ሲመነዘር ማየት ያስተዛዝባል። ፍትሕና እውነት ወገናዊ ሊሆኑ ፈጽሞ አይገባም። አባቶቻችን ያቆዩልንን የፍትሕን አተረጓጎም አዛብተን ለየግላችን አገልግሎት የሚውል የፍትሕ አሠራር መከተል ከጀመርን ለጉልበተኛ የሚመች ደንብ ፈጥረን የምንተላለቅበትና ማኅበራዊ ኑሮ የሚመሰቃቀልበት ሁኔታ እንደሚከሰት ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።

> "The good we secure for ourselves is precarious and uncertain until it is secured for all of us and incorporated into our common life." Jane Addams
>
> *"ለራሳችን ብቻ ብለን የምናስከብረው መልካም ነገር በጋራ የሚጠቅመን ሆኖ በጋራ ሕይወታችን ውስጥ እስካልተዋሀደ ድረስ የሚያስተማምን ሊሆን አይችልም።" ጀን አዳመሰ*

ከዚህ ዓይነት አመለካከት ወጥተን ለጋራ እድገት፣ ብልጽግናና ሰላማዊ ኑሮ እንድንበቃ ከፈለግን ከላይ የሰፈረው ጀን አዳምሰን ጥቅስ ታላቅ ምክር ነውና ሁላችን ልብ ልንለው ይገባል። **ፍትሕ ራሱ ባለው እሴትነትና ለአንድ ሕብረተ-ሰብ የጋራ ትስስር ሊኖረው ከሚችለው ጠቀሜታ አንጻር ተሰልቶ አገልግሎት ላይ ካልዋለ የሚከተለው አደጋ በቀላሉ የሚጠገን አይሆንም። በመሆኑም ለወንድምና እህት በሚሰጠው ነጠላ ጥቅም መመንዘር የለበትም፣ አደገኛ ነው።**

በዚህ ህዝባዊ የስልክ ስብሰባ ወቅት ሁለት ሰዎች ያልሆነ ምስክርነት ሲሰጡ ተደምጧል። ይኸውም፣ ሐጎስ ዮሐንስ አውቀውም ይሁን ተሳስተው፣ ቀደም ሲል ለኢሮብ መብት ተሟጋች

ማህበር (ኢ.መ.ተ.ማ) በጠራው ሐጎስ ዮሐንስ “ድብቅ” ባሉት ስብሰባ ላይ ከተቋቋመ አምስት ዓመት ማስቆጠሩን ገልጿል ይላሉ። ያ ነገር እንዳልተባለ ማስተባበያ ሲሰጥ ሁለት ከሳቸው ጋር የተቧደኑ ግለሰቦች አዎ እኛም ሰምተናል ከተቋቋመ አምስት ዓመት አስቆጥሯል ብላቹሃል በማለት ምስክርነታቸውን ሲሰጡ አድምጠናል። የተባለው እውነት አይደለም። የተባለው ዕለት የተካሄደውን የስልክ ስብሰባ የተመራው በዚህ ፀሐፊ ሰብሳቢነት ነው። በዕለቱ የተነሱ ነጥቦችንም በዝርዝር ይዞዋቸዋል። በመሆኑም እንደዛ አልተባለም፤ አንዳንድ ሰዎች የፈጠራ ወሬ ያወራሉ ማለት ሁሉም ሰው እንዲሁ እንደመጣለት ያወራል ማለትም አይደለም። በተባለው ዕለት በተካሄደው የስልክ ስብሰባ ላይ እንዲህ ዓይነት የሌለ ነገር ቢወራ ኖሮ ሰብሳቢው ያስተካክለው ነበር። እንዲህ ዓይነት ተራ ስሕተት ሲነሳ የመረዳትና መስመር የማስያዝ የተወሰነ ዓቅምምኝ ብሎ ያምናል። ዋናው ቁምነገር ግን ኢ.መ.ተ.ማ ከተመሠረተ ምን ያህል ዕድሜ አስቆጠረ? የሚለው አይደለም። ከተመሠረተ አልሆነም እንጂ ሃያም፤ ሳላሳም ዓመት ሊሆነው ይችላል። የተነሳለት ዓላማ የወራት ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ከተጨመረበት ለትውልዶች እንዲዘልቅ፤ ይበልጥ እየሰፋና እየጎመራ እንዲሄድ፤ ትውልዶች እየተቀባበሉ እያሻሻሉትና ከሁኔታና ጊዜ ጋር እያቀናጁ እንዲያስቀጥሉት የተወጠነ መልካም ጅምር በመሆኑ፤ ከተቋቋመ አምስት ዓመት አስቆጥሯል ብላቹሃል የሚለው ክስ የሚያስጨንቅ አይሆንም። ኢ.መ.ተ.ማ አምስት ዓመት ሲሞላው በይፋ አውጆ እንዲያከብረው እንመኝለታለን።

እዚህ ላይ ዋና ለማሳየት የተፈለገው “ኢኒ ማዕታባህ አሚስኪረ” ማለት “ለሂልናየ እውነትን እመሰክራለሁ” የሚለው የአበው ባህልና አባባል ቦታ መነፈጉን ነው። ኧረ ጎበዝ ምን ነክቶን ነው!! ኧረ እውነትን አንግፋት!!! እውነት አሁን የኢ.መ.ተ.ማ አምስት ዓመት መቆየት አጀንዳ መሆን ነበረበት?

ነገሩ የተፈለገው፤ ኢ.መ.ተ.ማ የፖለቲካ ድርጅት ነው ብለው ለሚያናፍሱት አሉባልታ ለማስረጃነት ይጠቅማል በሚል ስሌት የተወጠነ ውጥን ነው። እኛ ከአምስት ዓመት በኋላ ደረስንበት እንጂ በሕቡእ ራሱን ሲያደራጅ ነበር በማለት ህዝብን ለማደናገር ሆን ተብሎ የተጠነሰሰ ውዲት ነው። ይህ እነሱ የሚነዙት አሉባልታ በኢ.መ.ተ.ማ ዓላማ ውስጥ አልተንጸባረቀም። ለነገሩ ግን የኢ.መ.ተ.ማ አባላት የፖለቲካ ድርጅት ለማቋቋም ቢፈልጉ ነውሩ ምኑ ላይ ይሆን? እነዚህ ወዶ-ገብ ካድሬዎች እንደሚሉት ኢ.መ.ተ.ማ የፖለቲካ ድርጅት ለመመሥረት ቢፈልግ የሚያግደው ነገር ምን አለ? ኢትዮጵያ ውስጥም ውጭም የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳሸን እየፈሉ አይደለ እንዴ? ደግሞስ የወዶ-ገብ ካደሬዎች አሉባልታን እንደ እውነት እንኳ ቢወሰድ ውጭ አገር የሚኖሩ ሰዎች ሕቡእ የሚገቡበት ምክንያት ምን ይሆን? መቼም የውሸት ወሰን የለው! አልቃይዳ ናቸው ለማለት ይከጅላቸው ይሆን? መልሱን ማግኘት የሚቻለው ከነዛ ወዶ-ገብ ካድሬዎች ብቻ ነው። ለመሆኑ እነዚህ ወዶ-ገብ ካድሬዎች ራሳቸው የሚያምኑበትና የሚከተሉትን የፖለቲካ አጀንዳ ሲያራምዱ ሌላ ሰው የራሱን አመለካከት እንዳይገልጽ ለመከልከል የሚሯሯጡበት ምክኒያትና ሕጋዊ መሠረት ምን ይሆን? የኢትዮጵያን ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 31 አልነበብ ብሏቸው፤ ወይስ በፍላጎት እንጂ በሕግ መመራት የማይፈልጉ ትናንሽ አምባገነኖች እየተፈጠሩ እንዳይሆን ያሰጋል። “እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሳው” እንደሚባለው ለዛ አይበቁም እንጂ እነዚህ ወዶ-ገብ ካድሬዎች የሆነች ትንሽ ሥልጣን ቢያገኙ ኖሮ ምን ዓይነት ፍትሕ ሊሰጡን እንደሚችሉ ከወዲሁ ለማየት በቅተናል። የሆነ ሆኖ ዋናው እዚህ ለማስጨበጥ የተፈለገው ለምስክርነት የሚጠራ ሰው መመስከር ያለበት እውነትና እውነትን ብቻ መሆን እንዳለበት ነው። በመሆኑም፤ ይህ ፀሐፊ እባካቹህ የሚያስተዛዝበን ጉድ ውስጥ አንግባ፤ የአመለካከት ልዩነት ቢኖር በአገባቡ ከተጠቀምንበት ለእድገታችን ታላቅ እሴት ነው። ለተወሰኑ የማይረቡ ጥቅማጥቅሞች ሲባል በፈጠራ ወሬ እያናፈሱ የንጹሕ ሰዎች ስምና

ስብእናን መንካት ግን ወንጀል ነው። ይህ ሰውን ያራርቃል፣ ያጣላልና ሕብረተ-ሰባችን እነዚህን ወገኖች አደብ እንዲገዙ መምከር ይጠበቅበታል። በዚህ አጋጣሚ ኢ.መ.ተ.ማ የተመሠረተው በፈረንጆች አቆጣጠር ሜያዚያ 2009 እንደሆነና ሐጎስና መስካሪዎቻቸው አምስት ዓመት አደረገ ያሉበት ወቅት ከተቋቋመ ወደ ዘጠኝ ወር ይሆነው እንደነበረ መዘገቡ አንባቢ ግንዛቤ እንዲያገኝ ይረዳል።

ይህ ፀሐፊ ከላይ በስልክ ስብሰባዎች የነበሩ ክስተቶችንና የሐጎስ ዮሐንስ የፈጠራ ወሬ ያስከተለው ውዥንብርን በሚመለከት አመለካከቱን ለማስፈር ሞክሯል። ከዚህ ቀጥሎ የሐጎስ ዮሐንስን ፅሑፍ ተያይዞ ቀርቧል። አንባቢ ከዚህ በላይ የተፃፈውንና ከዚህ ቀጥሎ የሚሰፍረውን ሐተታ በሚገባ ለማገናዘብ ይችል ዘንድ እዚህ ተያይዞ የቀረበውን የሐጎስ ዮሐንስን ፅሑፍ እንዳለ አስቀድሞ ቢያነበው መልካም ይሆናል። የሐጎስ ዮሐንስን ጽሑፍ እዚህ ጋር ተያይዟል [1] (ጽሑፋቸውን ለማንበብ “ctrl” ን በመጫን ይክፈቱት)

ይህ ፀሐፊ ይህንን ፅሑፍ ለመተቸት የተነሳሳው የተጣመመውን ለማቃናት ይረዳ ዘንድ የተሰነዘረው የፈጠራ ወሬ ተጋልጦ ለህዝብ ይፋ እንዲሆን ጥሪ ለማቅረብ ነው። የሐጎስ ዮሐንስን ጽሑፍ አገባብ ባለው መልኩ መተቸት ስሕተትን ማረም፣ ታሪክን ማስተካከልና ሓላፊነትን እንደመወጣት በመቁጠር ነው። የሐጎስ ዮሐንስ የፈጠራ ወሬ የተወሰኑ ሰዎችን አላሳመነም ለማለት አይቻልም። ይህ እነዚህ ይሁንብን ብለው በወዶ-ገብ ካድሬነት ራሳቸውን በማሰለፍ የፈጠራ ወሬን ለማራገብ ቆርጠው የተነሳሱ ጨካኞችን አይጨምርም። እነሱ እውነትን ሸፍነው ውሸትን እውነት አስመስለው በሸፍጥ እሳት ለኰሰው ለማራገብ ቆርጠው የተነሱበት ዓላማ ነውና “እውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱትም አይሰማ” እንደሚባለው ቢነገራቸውም ለመስማት ዝግጁ እንዳልሆኑ ግልጽ ነው። ይህንን ዓይነት ዝግጁነት ቢኖራቸው መጀመርያውኑ በፈጠራ ወሬ ሰውን ለማባላት አይሞክሩም ነበር። በመሆኑም እነሱን የሚመለከት አይሆንም። ይህ ትችት በድረ-ገጽ ፅሑፍ በማውጣት፣ ስልክ በመደወልና Facebook የተባለውን ገጽ በመጠቀም የተነዛው የስም ማጥፋት ዘመቻ ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገቡ የተደረጉ ወገኖች ሐቁን እንዲያውቁ ለማድረግ ነው። ይህ አሁን የፈጠራ ወሬን ማምረት የጀመረው የወዶ-ገብ ካድሬዎች ቡድን ተጋልጦ እራቆቱን እስኪወጣ ድረስ በዚህ ተግባር መቀጠሉ ስለማይቀር፣ አንባቢ የሚነዙ ወሬዎችንና ጽሑፎችን በጥልቀት መርምሮ አውቆ፣ በአመክንዮ አስደግፎ እንዲቀበላቸው ወይም እንዲጥላቸው ለማሳሰብ ነው።

እንግዲህ ትችቱ እነሆ!

ፅሑፉ ውስጥ ስንገባ ሐጎስ ዮሐንስ “አሁንም ቢሆን ገና አንዳ አንድ እርስ በርስ የሚቃረኑ ስሜቶች በውስጤ አሉ” በማለት ጽሑፋቸውን እንደጀመሩ እናነባለን። ሚከተለውን ያክሉበታል፣

> “በአንድ በኩል ለወገኔ የኢሮብ ህዝብ በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ለመንገር የመፈለግ ስሜት አድሮብኛል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በብቃት፣ በጭብጥ አስደግፌ ራሴን ለመግለጽ መቻል አለመቻሌን ትንሽ እጠራጠራለሁ።”

ችግሩ ያለው እዛ ላይ ነው ሐጎስ ዮሐንስ። እውነትን ተመርኩዞ አለመነሳት ከሁሉም በፊት በራስ የመተማመን ግርማ ሞገስን ገፎ ውስጠ-ባዶ እንዲሆኑ ነው የሚያደርገው። ይህንን አውነት ደግሞ ገና ፅሑፉዎን ጀምረው ሶስተኛ መስመር ላይ እንደደረሱ በሚገባ እንደተገነዘቡት በፅሑፉዎ ውስጥ የሰፈረ ሃቅ ነው። ሶስተኛ መስመር ላይ “አሁንም ቢሆን ገና አንዳ አንድ እርስ በርስ የሚቃረኑ ስሜቶች በውስጤ አሉ” ሲሉ የጀመሩት የትም የሚያደርስዎት እንዳልሆነ ሲጀምሩ ጀምሮ

እንደገባዎት በግልጽ ያሳያል። በሆነ ምክንያት የማያምኑበትና የማያውቁት ችግር ውስጥ እጅዎን እየከተቱ እንደሆን አስቀድመው ተረድተውታል። አንድ ማስረጃና መረጃ አሰባስቦ በሚያውቀውና ማስረጃ በያዘበት ጉዳይ ላይ የሚፅፍ ሰው በሚፅፈው ነገር ላይ አይጠራጠርም። እርሶ ግን "...በብቃት፤ በጭብጥ አስደግፌ ራሴን ለመግለጽ መቻል አለመቻሌን ትንሽ አጠራጥሮኛል።" ብለዋል ከጅምሩ። እንዲህ ዓይነት እውነትን አስክዶ ጭንቀት ውስጥ በመክተት የፈጠራ ወሬን በመንዛት ለማግኘት የሚመኙት ነገር ምን እንደሆነ ከራስዎ በላይ የሚያውቀው ሰው አይኖርም። የራስዎ ጽሑፍ የሚመሰክረው አንድ ሃቅ ቢኖር ግን ያሰራጩት **የፈጠራ ወሬ** መሆኑን ነው። አንድን ነገር ለመግለጽ ብቃቱ ከሌለና በጭብጥ ለማስደገፍ ካልተቻለ መጀመርያውኑ ሊገባበት አይገባም ነበር። በመሆኑም ፅሑፉዎን ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ ልብ ብሎ ላነበበው ሰው ምንም የተጨበጠ ነገር ሳይዙ የገቡበት ጣጣ መሆኑን ለመገንዘብ ጊዜ አይወስድበትም። ፅሑፉዎ የሰዎችን መልካም ስም አጉድፎ ጥላሸት በመቀባት በሕብረተ-ሰባችን ውስጥ ወጅንብር ለመፈጠር ያደረገው አሉታዊ አስተዋፅዖ መኖሩ የማይካድ ነው። ከዛ የዘለለ ቁምነገር ግን የለውም፤ ሊኖረውም አይችልም።

የዛሬ መጣጥፍ ከመቋጨቱ በፊት "ከተከባበርን ሁሉም ይቻላል" በሚል ርእስ አቶ/ወይዘሮ (ይቅርታ ስሙ ለወንድም ለሴትም ሊሆን ስለሚችል ነው) ሙሉ በየነ በኢሮብ ማብሎ ያወጡትን ፅሑፍ አስመልክቶ አጭር አስተያየት መስጠቱ አስፈላጊ ይሆናል።

በማስቀደም ይህ ፀሐፊ አቶ/ወይዘሮ ሙሉ በየነ ለሰጡት አስተያየት ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል። ተሳትፎአቸው ሌሎችም የውይይቱ ተሳታፊ ለማድረግ ከማበረታታት አልፎ የምናካሂዳቸው ውይይቶች ጥልቀትና ስፋት እያገኙ እንዲሄዱ ስለሚረዳ እጅጉን የሚመሰገን ነውና ይበርቱበት።

ፅሑፍዎ ሀርበርት ሄነሪ ለህማን "ምንም እንኳ ባልስማማበትም የሌሎችን አመለካከት የማክበር ግዴታ አለብኝ" እንዳለ ጠቅሷል። ይህ ጥቅስ እንዲህ በድፍኑ ሲታይ እጅግ ጠቃሚና ሁሉም ሊከተለው የሚገባ መልካም አባባል ነው። ሙሉ በየነም ጥቅሱ የያዘው አጠቃላይ መልእክትና ይዘቱን በማካፈላቸው ሊመሰገኑ ይገባል። ይህ ፀሐፊም የአመለካከት ልዩነት እጅጉን መከበር ያለበት ታላቅ እሴት መሆኑንም ይቀበላል። ከዚህም አልፎ የተለያዩ ሃሳቦች፤ ግኝቶችና አመለካከቶች መኖር ለአንድ ሕብረተ-ስብ እድገት ወሳኝ ተራ አላቸው ብሎም ያምናል። ሙሉ በየነና ይህ ፀሐፊ በዚህ መሠረተ ሐሳብ ላይ ልዩነት የሚኖራቸው አይመስልም። ልዩነቱ የሚመጣው ውሸት፤ ቅጥፈት፤ የፈጠራ ወሬ፤ አሉባልታ፤ የሌሎች ሰዎች አመለካከቶች ናቸውና ባልወዳቸውም መከበር አለባቸው ብሎ ይህ ፀሐፊ ፈጽሞ አያምንም። ሰዎች አንድ ነገር ለማድረግ ቢያስቡ ያንን ለማሳካት የሚሄዱበት መንገድ ሊለያይ ይችላል። ይህ ዓይነት ልዩነት ላይ ተከባብሮ የየራስን አጀንዳ ማራመደ ተገቢና ሊገፋበት የሚገባ መልካም አርአያ ነው። በዚህ ላይ ልዩነት የለም። ነጭ ውሸትና እውነት መካከል ያለው ልዩነት ግን እንደ አመለካከት ልዩነት ተደርጎ መወሰድ በፍጹም የለበትም። ይህ ዓይነት አጀንዳ በመቻቻል የሚፈታም አይደለም።

ሙሉ በየነ የሐጎስ ዮሐንስ ፅሑፍ ይዘት የአመለካከት ልዩነት ነው ብለው የሚያምኑ ከሆነ፤ እርስዎና ይህ ፀሐፊ መካከል የትርጉምና የአመለካከት ልዩነት አለ። ሐጎስ ዮሐንስ ለህዝብ ይፋ ያደረጉት ተራ የፈጠራ ውንጀላ እንጂ በአመለካከት ልዩነት ማእቀፍ ውስጥ ሊታይ የሚችል ይዘት ያለው አይደለም። ይህንን ዓይነት ፈጠራ አባቶቻችን ባቆዩልን ባህልም ውጉዝ እንጂ እንደ አመለካከት ልዩነት ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም። የሆነ ሆኖ ፅሑፉን አንባቢ እንዲፈርደው ተያይዞ ቀርቧል። ፍረዱንም የሚሰጠው አንባቢ ይሆናል። ሐጎስ ዮሐንስና ተከታዮቻቸው

ሕወሓት/ኢህአዴግ የሚያራምደው ፖለቲካን ደግፈው ይሰብካሉ። ለምን ወዶ-ገብ ካድሬዎች ሆናቹህ ብሎ የሚከሳቸው ሰው መኖር የለበትም። ይህ የማይገሰስ መብታቸው ነው፤ አንዱ ወደደው ጠላው መከበር ያለበት ነውና መከበር አለበት። የኢሮብ ወጣቶችን ለሻዓቢያ የሚመለምሉ የኢሮብ ተወላጆች አሉ ማለት ግን የአመለካከት ልዩነት ሳይሆን ከፍተኛ ውንጀላ ነው። በመሆኑም ሀቁ እስካልወጣ ድረስ የሚፈታ አይሆንም። እዚህ ውስጥ መከባበር አለመከባበር የሚባል ነገር የለም። ይህንን እንደ ልዩነት ተመልክተህ አክብር የሚባል ከሆነምጸ ይህ ፀሐፊ ለርስዎ የሚኖሮው አክብሮት ሳይቀንስ፤ ይህ የአመለካከት ልየነት አለመሆኑን ከላይ አስፍሯልና ለመቀበል እንደማይችል ለማስታወስ ይወዳል። ይህ ተራ ውንጀላ እንጂ አመለካከት አይደለም፤ ውንጀላን ውንጀላ ነው ማለት ደግሞ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው ብሎ ይህ ፀሐፊ ያምናል።

ካድሬና ርካሽ ተንኰል የሚሉ ቃላቶች ለሰሚም ክብር እንደሌላቸው አስፈሯል። ይህ ፀሐፊ ሁሉን በስሙ መጥራት ነውር የለውም ብሎ ያምናል።

ለዛሬ "ኮሕያው ሓባ ኖድማዳጊናዬ….." የሚለውን ዘፈን ለአንባቢ መርጦ ይሰናበታል።

የሳምንት ሰው ይበለን፤ መልካም ሳምንት ለሁሉም!!!

ይቀጥላል…………

የካቲት 12 ቀን 2011 ዓ.ም.ፈ